## በማህበረሰብዎ ውስጥ

“የ Community Food Rescue (የማህበረሰብ ምግብን ማዳን) የማዛመድ ፕሮግራም እንደ እኔ ላሉ አነስተኛ አምራቾች ምርታችንን ሊጠቀሙበት ለሚችሉ ማድረስን ቀጥተኛ ያደርገዋል። ይህም ለእኔ በማይታመን ሁኔታ ቀላል እና አርኪ ነበር እናም ከማህበረሰቤ ጋር እውነተኛ ግንኙነት እንዳለኝ እንዲሰማኝ ረድቶኛል።”

Amanda Cather፣ ገበሬ፣ Plow and Stars Farm





## ስለ የማህበረሰብ ምግብ ማዳን

Community Food Rescue (CFR፣ የማህበረሰብ ምግብ ማዳን) በ Manna Food Center (ማና የምግብ ማእከል) የሚቀናጅ መረብ ነው። በአካባቢው የምግብ መልሶ ማግኛ ግብረ ኃይል አነሳሽነት፣ Community Food Rescue በየቀኑ ያልተሸጠ ወይም ትርፍ ምግብን ለማዳን እና ረሃብ እያጋጠማቸው ላሉ ሰዎች መልሶ ለማከፋፈል የማህበረሰባችን ኢጋር ይሆናል እንዲሁም አቅሙንም ይገነባል። ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ንግዶችን እና ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶችን አጋሮቻችን አድርገን ስንቆጥር ኩራት ይሰማናል።

CFR ሊካሄድ የቻለው በ Montgomery County Department of Health and Human Services (በሞንትጎሜሪ ካውንቲ የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎቶች መምሪያ እንዲሁም በግል ለጋሾች፣ በጎ ፈቃደኞች እና የተሳታፊ ድርጅቶች ቁርጠኛ ሰራተኞች ቸር ድጋፍ አማክኝነት ነው።

ለበለጠ መረጃ እና እኛን ለመቀላቀል፡-
**www.communityfoodrescue.org**
**www.facebook.com/communityfoodrescue**
**@mocofoodrescue**

አድራሻ፡- Cheryl Kollin, CFR Program Director
**cheryl@communityfoodrescue.org**
240.268.2502

“ የተደጎመ ምግብ ስንቀበል በጀታችን ተጨማሪ ብዙ ይሄዳል። የ CFR የማዛመጃ መረብ ይህንን ምግብ የመቀበሉን ፈተና በጣም ቀላል ያረገዋል።“

ሃይሌ ገብረእግዚያብሄር፣
የከወናዎች ዳይሬክተር፣
Shepherd’s Table



# ብዙ ይመግቡ፣ ትንሽ ያባክኑ

## ረሃብን መዋጋትን ለማገዝ ምን ማድረግ ይችላሉ

Community Food Rescue
because food is a terrible thing to waste



# Community Food Rescue (CFR) በሜሪላንድ የሞንትጎሜሪ ካውንቲ የተቀናጀ የምግብ መልሶ ማግኛ መረብ ነው።

በሞንትጎሜሪ ካውንቲ፣ ከአጠቃላዩ ደረቅ ቆሻሻ 146,000 ቶን (23%) ያህሉ የምግብ ቆሻሻ ነው እንዲሁም ከነዋሪዎቹ 78,000 ያህሉ ቀጣዩ ምግባቸው ከየት እንደሚመጣ አያውቁም። *

## CFR ከቆሻሻ ማከማቻዎች ይልቅ እንዴት ሰዎችን እንደሚመግብ የሚያሳዩ ታሪኮች፡-

- የሞንትጎሜሪ ካውንቲ የማህበረሰብ ፋውንዴሽን የምግብ አቅራቢያቸውን ከአመታዊው የእራት ግብዣ የሚተርፈውን እንዲለግሱ ጠየቀ። Tropical Fusion Caterers ጣፋጩን አለም አቀፋዊ ምግብ ለ Bethesda Cares ደንበኞች ለግሶ በልዩ ምሳውም ደስተኞች ነበሩ።

- Star and Plow Farm የ CFRን ማዛመጃ መሳሪያ በመጠቀም 200 lbs. ትርፍ ኦርጋኒክ ቲማቲም ለልገሳ አቅርበው ነበር። ልገሳውም ወዲያውኑ ከ Shepherd's Table እና ትኩሱን ምርት ካጓጓዘው በጎ ፈቃደኛ ምግብ አድራሽ ጋር ተዛምዷል። Shepherd's Table ቲማቲሞቹን በስጎ መልክ አብስሎ በሚቀጥለው ምሽት ለ120 ቤት አልባ እንግዶች አቅርቦታል።

- Manna Food Center በየቀኑ በአማካይ 7000 ፓውንድ ያህል ጤናማ የሆኑ ግን ሊሸጡ የማይችሉ ምግቦችን Giant፣Safeway፣ Wegmans፣ Food Lion፣Harris-Teeter፣ Fresh Markets፣ Whole Foods፣ Mom's Organic Market፣ Trader Joe's እና Shop Rite and Roots ጨምሮ ከ 50 በላይ የሞንትጎሜሪ ካውንቲ የምግብ መሸጫ አካባቢዎች ይታደጋል። ይህ የተሰበሰበ ምግብ በአመት Manna ከ 38,000 ለሚበልጡ የአካባቢ ነዋሪዎች ለሚያከፋፍለው ምግብ 16,000 ፓውንድ የቀን አማካይ አስተዋጽኦ ያደርጋል።

## Community Food Rescue የሚከተሉትን ያቀርባል፡-

- ነጻ ራስ ሰር የማዛመጃ መተግበሪያ። የተመሳሳይ-ሰዐት ቴክኖሎጂ የምግብ ለጋሾችን፣ የምግብ እርዳታ ድርጅቶች እና የምግብ አድራሾችን ያልተሸጡ ትርፍ ምግቦችን ወደ ሌላ ማዛወር እንዲችሉ ያዛምዳል።

- የህዝብ እውቅና ፕሮግራም። አብረው የሚሰሩ ለጋሾችን እና ኤጀንሲዎችን በህዝብ እውቅና ፕሮግራማችን እናከብራለን። ሸማቾች  መልሰው ለህዝቡ የሚሰጡ የንግድ ተቋሞችን በቀላሉ መለየት ይችላሉ።

- መረጃ እና መርጃዎች። በነፃ መመሪያዎቻችን፣ በቪዲዮዎች፣ በብሮሸሮች፣ በስልጠና ክፍለ ጊዜዎች እና በድረ ገጽ ምንጮች በኩል አስተማማኝ የምግብ አያያዝ እና የትራንስፖርት መስፈርቶችን እናካፍላለን።

- ልዩነት የመፍጠሪያ እድል። በ Community Food Rescue በኩል ጊዜን ወይም ምግብን በመለገስ፣ የቆሻሻ ጉርጓድ ቦታን ለመቀነስ እንዲሁም ረሃብ እያጋጠማቸው ያሉትን ሰዎች ማጀት ለመሙላት ያካባቢ ነዋሪዎች የአካባቢ ነዋሪዎችን ያግዛሉ።

"እየሰራ ነው!"

ሼፍ Tony Marciante፣ የ Tony Restaurant ሼፍ፣ የ CFRን የድረ ገጽ መተግበሪያ በተመለከተ ጊዜ የመጀመሪያውን የምግብ ልገሳ ከ Interfaith Works–Carroll House ጋር አገናኝቷል።

* የሞንትጎሜሪ ካውንቲ የተረፈ ምርት ጥንቅር ጥናት July 26, 2013 እና የአሜሪካን ካርታ መመገብ - የምግብ ክፍተት ጥናት 2015።











## እንዴት ብዙ መመገብ እና ጥቂት ማባከን ይችላሉ።

### ምግብ ለጋሽ የንግድ ተቋማት

እንደ ምግብ አዘጋጆች፣ ገበሬዎች፣ የገበሬዎች ገበያዎች፣ ግሮሰሪዎች፣ ተቋማት፣ ሬስቶራንቶች፣ወዘተ... ያሉ በሞንትጎሜሪ ካውንቲ ፍቃድ ያላቸው የምግብ ንግድ ተቋማት፡-

- የተሻሻለ የታክስ ቅነሳ ይውሰዱ
- በእኛ የህዝብ እውቅና ፕሮግራም ንግድዎን ይለዩ።
- በ Federal Good Samaritan Act (ፌዴራል ጥሩ ሳምራዊ ህግ) በኩል ተጠያቂነት ይከላከሉ።
- የሞንትጎሜሪ ካውንቲን በ 2020 70% መልሶ ጥቅም ላይ የማዋል ግብን ለማሳካት ያግዙ።

### የምግብ እርዳታ ድርጅቶች

ረሃብ እያጋጠማቸው ላሉ ሰዎች ምግብ የሚያቀርቡ የረሃብ እርዳታ ድርጅቶች።

- ትርፍ የሆኑና የተለገሱ ምግቦችን በመጠቀም ከምግብ በጀትዎ ላይ ይቆጥቡ።
- ሊቀበሉ በሚችሉት የምግብ ጥራትና መጠን መሰረት አዳዲስ የምግብ ምንጮችን ከተለያዩለጋሾች ይቀበሉ
- Montgomery County's Department of Health and Human Services (በሞንትጎሜሪ ካውንቲ የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎቶች መምሪያ) በኩል ተቀባይነት ያገኙ አስተማማኝ የምግብ አያያዝ ልምዶችን ይወቁ።
- የእርስዎ ድርጅት መፍጠር የቻለውን ተጽዕኖ ለለጋሾች ለማሳየት እንዲረዳው፣ ድርጅትዎ የለገሰውን ጠቅላላ የምግብ መጠን ማጠቃለያ ሪፖርቶች ይቀበሉ።

### በጎ አድራጊ ምግብ አድራሾች

በጎ አድራጊዎች፣ 18 አመት እና ከዚያ በላይ የሆናቸውና መኪና የያዙ፣ ጥሩ የማሽከርከር ሪኮርድ፣ እንዲሁም የተለገሰውን ምግብ ከንግድ ተቋሞቹ ወደ ተቀባይ የምግብ እገዛ ድርጅቶች ማጓጓዣ የተሽከርካሪ ዋስትና፡-

- ረሃብ እያጋጠማቸው ያሉ ጎረቤቶችን ይርዱ እንዲሁም የምግብ ብክነትንም ይከላከሉ።
- ስለ አስተማማኝ የምግብ አያያዝ፣ -ማጓጓዝ እና የምግብ ቅነሳ ልምዶች ይማሩ።
- ብዙ ለመመገብ እና ትንሽ ለማባከን ከመላው ቤተሰብዎ ጋር፣ ጉባኤ ወይም የማህበረሰብ ቡድን ጋር ይሳተፉ።